# ቅሪብን አንቺስ አትምጪብን

ሆሆ! ሆይ! ገዳማይ ገደምዳማዬ
ብርቱካን ሚደቅሳም ወይናለች ወይ!?
ሆሆ! ሆይ! ገዳማይ ገደምዳማዬ

ብለናት እንዳልነበር ሴቲቱ አንበሳ
ሆና እኮ ተገኘች የብርሃኑ እንቦሳ
በህዝብ ላይ ቆርጣ ልታመጣ አበሳ።
ብትል እንጣጥ፣እንጣጥ ሆና ሐሰተኛ
እውነቱ እስኪወጣ እኛም አንተኛ።

ብርቱካን አልሆንሽም የምትጣፍጪ
ግን ቆምጣጣ ከሆንሽ የምትበጠብጪ
እግርሽ ይያዝልን ወደኛማ አትምጪ።
ባለአሞሌው አይችል፣ያልቻለውን ባለዕዳ
አርፈን በተቀመጥን ችለን የስድብ ናዳ
ልትበታትኚን አትምጪ ካናዳ።

ምን ልትፈጥሪ ነው!? ቫንኩቨር፣ካልጋሪ
መሪሽን ረግጠሽ ሳታነጋግሪ
እትዬ ፈጠነች እንዲሁ አትብረሪ።
ምንስ ያለፋሻል ዊኒፔግ፣ቶሮንቶ
ለማፍረስ ካልሆነ በህብረታችን ቀንቶ
ፓልቶክ እኮ አለልሽ ለነገር ባዘቶ
ሲሳደብ የሚውል ከረንት ተጎልቶ።
ዘግተው ሲጯጯሁ ከቶ መቼ ሰሙን
እዛው ያስተናግዱሽ ለእስር ቤት ሀኒሙን።

ማይጨው ወንጀለኛው፣ሻቢያው እንደልቡ
ሱሰኛዋ ሙያዬ፣ ቆለኛው ሲገቡ
እስቲ እንዳዬን አዬን የኛም ሊያራግቡ
ጳውሎስ የላከው ወያኔው የገብርኤሉ
ብርሃኑ ነጋ፣ተወርዋሪውና ደግሞም ጎሹ ጅሉ
ቀሎ ለመዋረድ ምንም አታስቢ እነሱ እያሉ።

ስለዚህ ፈጠነች ቅሪብን፣ ቅሪብን
ልትበታትኚን ካናዳ አትምጪብን።

ከሚካኤል ሰይፉ (ቶሮንቶ፤ካናዳ)